| | | |
|---|---|---|
| | | |
| **የሥራዝርዝርመግለጫቅጽ** | | |
| **I.** አጠቃላይመግለጫ | | |
| የመስሪያ ቤቱ ስም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት |
| የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | ነርስ ፕሮፌሰናል II | ነርሲንግ |
| | | |
| የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት | በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር/ቢሮ ብቻ የሚሞላ | |
| | የሥራው ደረጃ | የሥራው ኮድ |
| የክፍሉ ሃላፊ ነርስ/ነርስ ሱፐርቫይዘር | XII | |
| | | |
| መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ | | |
| በየደረጃው ባሉ የጤና ተቋማት | | |
| **II.** የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ውጤቶችና ተግባራት | | |

**2.1.** የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- የህሙማን መረጃና የህክምና መገልገያ ግብዓቶችን ለሥራ ዝግጁ በማድረግ፤ የህሙማን ክብካቤ ሥራዎችን በማቀድና በመስራት፣ አፈጻጸሙን በመከታተልና ለችግሮች የመፍትሔ ሃሳብ በማቅረብ፣ የምክር አገልግሎት በመስጠት፤ የተሻሉ ተሞክሮዎችን በመቀመር ደረጃውን የጠበቀና ርህራሄ፣ ጥንቃቄና አክብሮት የተሞላበት የነርስ ክብካቤ አገልግሎት እንዲኖር ማስቻል ነው።

**2.2.** የሥራ መደቡ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፣ የህሙማን መረጃና የህክምና መገልገያ ግብዓቶችን ለሥራ ዝግጁ ማድረግ።

- የህሙማን አጠቃላይ ሁኔታና የህክምና መገልገያ ዕቃዎችን ከተረኛው በጽሑፍና በቃል ይረከባል፣ ያስረክባል፤
- በሥራ ክፍሉ ውስጥ ለቀንና ለማታ የሥራ ፕሮግራም ለሕሙማን ክብካቤና ሕክምና የሚያስፈልጉትን መድሐኒቶች፤ መሣሪያዎችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን በበቂ ሁኔታ እንዲሟሉ ያደርጋል፤
- በሥራ ክፍሉ የሚገኙ ንብረቶች ዝርዝር ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ይመዘግባል፣ ደህንነታቸውንም ይከታተላል
- መረጃዎችን በኮምፒዉተር ይመዘግባል ሪፖርት ይቀባበላል የህመምተኛዉን ሚስጥር በጠበቀ መልኩ መረጃ ይለዋወጣል።

ውጤት **2**፣ የነርስ እንክብካቤና የምክር አገልግሎት መስጠት።

- የህሙማንን ክፍል ንፅህና ይጠብቃል፣አልጋ ያነጥፋል፣ የተባለሹ የህሙማን አልባሳትን ያስወግዳል፤
- በራሳቸው የግል ንፅህና መጠበቅ ለማይችሉ የተኙ ህሙማን በመኝታቸው ላይ እንዳሉ ሰውነታቸውን ያጥባል፣ ባከ ኬር፣ ይሰጣል፣ ህሙማንን ይመግባል፤በራሳቸው መመገብ የማይችሉትን ይመግባል
- የቁስል ክብካቤ ይሰጣል (ያጸዳል፤ይሰፋል፤ክሩን ያወጣል)
- የተለያዩ በነርስ የሚሰሩፕሮሲጀሮችን ከጨቅላ ህጻን እስከ ሽማግሌ በየደረጃቸዉ ይሰራል ( የሽንት ቱቦ፤የአፍንጫ ቱቦ፤የመተንፈሻ መርጃ

መሳሪያዎችን በመጠቀም)

- መድኃኒቶችንና የህክምና ዓይነቶችን ለህሙማን ይሰጣል፣ የታማሚውን ሁኔታ በመከታተል ለሐኪሙ ገንቢ አስተያየቶችን ያቀርባል፤
- ለህሙማን ክብካቤ ያደርጋል፣ የህሙማንን የጤና ሁኔታ በመከታል መፍትሔ ይሰጣል፤ ለምሳሌ ተላላፊ እና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታች እንደ ደም ግፊት፤ስኳር ግንዛቤ ያስጨብጣል፣
- በድንገተኛ አደጋ ወቅት ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመሆን የህይወት አድን ተግባራትን ያከናውናል፤ከአቅም በላይ ሲሆን ያማክራል፣
- በተመላላሽና ተኝቶ ህክምና የሚታከሙ ሕሙማንን ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን ሁኔታ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር ያመቻቻል፤
- ቤተሰቦቻቸው ለሕሙማን ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያደርጉ ያበረታታል፣ ይመክረል፤ ያጽናናል፣ያስተምራል፣

- ህሙማን በህክምና ላይ እያሉ ህይወታቸው ቢያልፍ አሰፈላጊውን የአስክሬን ክብካቤ ያድረጋል፤ አስክሬኑንም ወደ ማረፍያ ሞርግ ያድርሳል፤መረጃዎችን በመመዝገብና በጥንቃቄ በመያዝ ለሚመለከተው ኃላፊ ያስረክባል፣
- በተፈጥሮ እና ሰዉ ሰራሽ አደጋዎች ላይ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን በጋራ የመከላከልና የመቆጣጠር ስራ ይሰራል፣

ውጤት 3፣ የነርስ አገልግሎት አሰጣጥ ውጤታማ ለማድረግ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ።

- በሥራ ክፍሉ ውስጥ የሚሰጠው የነርስ አገልግሎት የሚጠበቀውን የቴክኒክ ጥራትና ደረጃ ይዞ መሄዱን ይገመግማል፣ አስፈላጊ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰድም ሃሳብ ያቀርባል፤ ይሰራል
- የነርስ አገልግሎት አሰጣጥን ውጤታማና ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም ሙያውን ለማሻሻል በሚደረጉ ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፤የራሱን ግብአት ያበረክታል
- የነርስ ተግባራት አፈጻጸም ሂደት ተከትሎ የታማሚውን ፍላጎትና የጤንነት ደረጃ በመለየት ምቹ ሁኔታ እንዲኖር ሃሳቦችን ያቀርባል፤
- ከሌሎች የጤና ባለሙያዎች ጋር በመሆን ለተገልጋዩ የተሠጠው የጤና ክብካቤና ህክምና አገልግሎት እንዲሁም የጤና ትምህርት ውጤታማነት ይገመግማል፤ያማክራል፤ያሻሽላል፣

ውጤት 4፣ የትምህርትና ሥልጠና ድጋፍ መስጠት።

- ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ለሚመጡ የነርስ ተማሪዎች የተግባርና የልምምድ ድጋፍ ይሰጣል፤ያሰለጥናል፣
- የደረጃ አንድ ባለሙያዎችን ሱፐርቫይዝ ያደርጋል ግብረ መልስ ይሰጣል፤
- ለህብረተሰቡ የጤና አጠባበቅ ትምህርት የሚሰጥባቸውን ርዕሶች ይለያል፤ የሥልጠና ማኑዋል ዝግጅት ላይ ይሳተፋል፤ይሰራል

ዉጤት 5 ጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ መሳተፍ።

- ከተገልጋዩ በተሰጠው ግብረ መልስ መሠረት የነርሲንግ አገልግሎት አሰጣጡን በመገምገም ተገቢውን ማሻሻያ ያደርጋል፤
- ሙያዉን በተመለከተ ችግር ፈቺ ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፤የራሱን አስተዋጾ ያበረክታል
- የነርስ አገልግሎት አሰጣጥንና ሙያን ለማሻሻል በሚካሄዱ ጥናቶች፣ የምክክር መድረኮች እና በነርስ ሥርዓተ ትምህርት ክለሳና ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ጠቃሚ ግብዓቶች ይሰጣል፤

- በተቋሙ የነርስ አገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ግምገማና ኦዲት ላይ ይሳተፋል፣ የአፈጻጸም ማሻሻያ ሃሳቦችን ያቀርባል፤
- ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።
- የአልግሎት ጥራት ስራዎች ላይ ይሳተፋል፤የጥራት ችግሮችን ይለያል፤የተለያዩ ክፍሎች ጋር በመሆን መፍትሄ ላይ ይሰራል፤

## III. የሥራው ባህሪ መገለጫዎች

### 3.1 የሥራ ውስብስብነት

- ሥራው የነርስ ክብካቤ ተግባራትን ማቀድና መተግበር፣ ለሥራ ክፍሉ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና ግብዓቶችን በመለየት እንዲሟሉ ማድረግ፣ በአፈጻጸም ላይ የሚያጋጥሙ ልዩ ልዩ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ሃሳብ ማቅረብ፣ ለህሙማን ክብካቤ፣ ምርመራ፣ ህክምናና ምክር ለነርስ ተማሪዎች የተግባር ልምምድና ምክር መስጠት፣ በጤና ነክ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና መስጠት እንዲሁም በመመሪያ፣ ማኑዋልና ፎርማቶች ዝግጅት መሳተፍ፣ በነርስ አገልግሎት ሙያ ማሻሻያ ጥናቶች፣ የምክክር መድረኮች እና በነርስ ሥርዓተ ትምህርት ክለሳና ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ጠቃሚ ግብዓቶች መስጠት፤ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ሥራ ላይ ማዋልን፣ ተላላፊና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች እንደ አጣዳፊነቱ አፋጣኝ እርምጃዎች መዉሰድ እርዳታ መጠየቅ፤ ማማከር፤ ከተለያዩ ከሚመለከታቸዉ ክፍሎች ጋር በጋራ መፍትሄ መፈለግ፤ ሥራው በሚከናወንበት ወቅት የባለሙያን የእዉቀት ደረጃ ግምት ዉስጥ በማስገባት ስልጠና ማመቻቸት፤የሚጠይቅ ሲሆን፣
- ሥራው በሚከናወንበት ወቅት ታካሚው ስላለበት የጤና ችግር የተሟላ መረጃ አለመስጠትና የሚታዘዝለትን መድኃኒትና የህክምና ምክር በአግባቡ አለመፈጸም፣ ተሞክሮዎችና የማሻሻያ ሃሳቦች ተቀባይነት አለማግኘት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ለውጥ ሥራዎችን ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን፣ ቤተሰብ ህመምተኛውን በአግባቡ አለመንከባከብ የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው።

- እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በጥሩ ሁኔታ ቀርቦ የህክምናን ጥቅም ማስረዳት፣ ክትትልና እንክብካቤ በማድረግ፣ የነርስ አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በመለየትና መፍትሔዎችን በማፍለቅ ማሻሻያ ማድረግ፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከርና በማሳመን ፈጣን ምላሽ መስጠት እንዲሁም የተለያዩ አማራጮችን ማቅረብና የተሻለውን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል።

### 3.2 ራስንችሎመስራት

#### 3.2.1 ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው የነርስ ክብካቤ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ፣ መመሪያ፣ የሥራ ወሰን፣ የአሠራር ማንዋሎችንና የሙያውን ሥነ ምግባር መሠረት በማድረግ ከቅርብ ኃላፊ በሚሰጥ አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ይከናወናል።

#### 3.2.2 ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ

- ሥራው ተፈላጊ የነርስ ክብካቤና የህክምና አገልግሎት ጥራትና ደረጃ ጠብቆ ስለመከናወኑ በመጨረሻ **በኃላፊው ይገመገማል።**

### 3.3 ተጠያቂነት

#### 3.3.1 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት፤

- የህሙማንን ክብካቤ ተግባራት ዕቅድ ዝግጅት፣ በአሠራር ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ሃሳቦችን በወቅቱ ባይቀርቡ፣ ለሥራ ክፍሉ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችና ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ ባያሟላ፣ ለህሙማን ክብካቤ፣ የምርመራ፣ የህክምናና የምክር አገልግሎት በወቅቱ ባይሰጥ፣ የህሙማንን ሁኔታ በመከታተል ለሐኪሙ ገንቢ አስተያየት ባያቀርብ፣ህብተሰረቡን የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ላይ ቅድመ ጥንቃቄ የማንዛቤ ማሰጨበጨጫ ስራ ባይሰራ፤ ለሚመለከታቸው አካላት የትምህርትና ሥልጠና ድጋፍ ባይሰጥ፣ እንዲሁም በማሻሻያ ጥናቶች፣ የምክክር መድረኮች እና በነርስ ሥርዓተ ትምህርት ክለሳና ዝግጅት ላይ በመሳተፍ ጠቃሚ ግብዓቶች ባይሰጥ፤ የተሻሉ የአሠራር ስልቶችን በመቀየስና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ተግባራዊ ባያደርግ ተጠቃሚዎች ጥራቱን የጠበቀ ነርሲንግ አገልግሎት አያገኙም፣ እስከ ሞት የሚያደርስ ጉዳት ሊያጋጥም ይችላል፣ **የጤና አጠባበቅ** አገልግሎት አሰጣጡን በማስተጓጎል በተቋሙ ሥራ አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡

**3.8.2.** ተጠያቂነት ለሚሰጥራዊ መረጃ

- ***ሥራው የታማሚውን የጤና መረጃዎችን በሚሰጢር መያዝ የሚጠይቅ ሲሆን መረጃው ለማይመለከተው አካል ተላልፎ ቢሰጥ በተጠቃሚው ላይ የሥነ ልቦና ቀውስ የሚያደርስበት ሲሆን በሙያተኛውና በተቋሙ ላይ ተአማኒነትን ያሳጣል፣*** በተቋሙና በአገልግሎት ተጠቃሚዎች መካከል ቅራኔና አለመግባባት ይፈጥራል፡

**3.8.3** ፈጠራ

- ሥራው በአፈጻጸም የታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የመፍትሔ ሃሳቦችን በማመንጨት፣ ማሉዋሎችንና ቅጾችን በማሻሻል፣ አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ፣ የነርስ ክብካቤአገልግሎት ርህራሄ፣ አክብሮትና ጥንቃቄ የተላበሰና ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይጠይቃል።

**3.5.** የሥራ ግንኙነት

**3.5.1** የግንኙነት ደረጃ

- ሥራው ከውስጥ ከቅርብ ኃላፊ፣ ከክፍሉ ሙያተኞች፣ ከሌሎች የሥራ ክፍል ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ ከላብራቶሪ፤ ከኤክስሬይ፣ ፊዝዮቴራፒና ከቀዶ ህክምን ከማህጸን ክፍል ክፍሎች እንዲሁም ከውጭ ከታካሚውና ከቤተሰቦች፣ከደምባንክ፤ከድንገተኛና እሳት አደጋ ለትምህርት ከሚመጡ ተማሪዎችና መረጃ ከሚፈልጉ አካላት፣ ከሚመለከታቸው የጤና ተቋማትና ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት አለው።

**3.5.2** የግንኙነቱዓላማ

- **ዕቅድ፣ ሪፖርትና የመፍትሔ ሃሳቦችን ለማቅረብና ለመወያየት፣ መረጃ ለመለዋወጥና አብሮ ለመሥራት፣ ለተገልጋዩ ጉዳዬችን ግልጽ ለማድረግ፣ የጤና ችግሮችን ለመፍታት፣ የምክር፣ የትምህርትና ሥልጠና ድጋፍ ለመስጠት፣ የጥናት ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ፣ ለድጋፍና ምክር እንዲሁም ተሞክሮ ለማግኘት ነው።**

**3.5.3** የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- የግንኙነቱ ድግግሞሽ ከቀን የሥራ ጊዜው 60 በመቶ ይሆናል።

**3.6** ኃላፊነት

**3.6.1** ኃላፊነት ለሰው ሀብት

**3.6.1.1** በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- የለበትም

**3.6.1.2** የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- የለበትም

**3.6.2** ኃላፊነት ለንዋይ

- የለበትም።

**3.6.3** ኃላፊነት ለንብረት

- ለሥራው የሚያገለግሉ ግምታቸው ብር 500,000.00 ብር የሆኑ እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ኮምፒውተር እንዲሁም ለህክምና አገልግሎት መስጫ የሚጠቀምባቸው የደም ግፊት፣ የሙቀትና የደም ውስጥ ኦክስጂን መለኪያ፣የደም ዉስጥ ስኳር መጠን መለኪያ፣ ሳክሽን ማሽን፣ ኦክስጂን ፍሎውሜተር፣ፔሸንት ሞኒተር፤አልትራሳዉንድ የተለያዩ ፕሮስጀሮች መስሪያ መሣሪያዎች፣ በአግባቡ በመያዝ የመጠቀም ኃላፊነት አለበት ጽኑ ጎሙማን ክፍል፤ጨቅላ ህጻናት፤ክፍል ተመድቦ ሊሰራ ይችላል ።

**3.7.** ጥረት

**3.7.1** የአዕምሮ ጥረት

- ሥራው ዕለታዊ የህሙማን ክብካቤና ክትትል ተግባራትን ማቀድና መፈጸም፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ሃሳቦችን ማዘጋጀት፣ መረጃዎችን መተንተን፣ የመመሪያ፣ የማኑዋልና የፎንማቶች ማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ፣ የሥልጠና ማዋሎችን ማዘጋጀትና ትምህርትና ሥልጠና መስጠት፣የታካሚውን የጤና ችግር ዓይነትና ደረጃ በአግባቡ በመለየት መፍትሔ መስጠት፣ በድንገተኛ በሽታዎችና ጉዳቶች ለሚመጡ ተገልጋዮች ፈጣን የህክምና ዕርዳታ መስጠት፣ መዲኃኒቶችን በመለየት በአግባቡ መስጠት፣ አስፈላጊውን የጤና አጠባበቅ ምክርና ክትትል ማድረግና ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሔ መስጠት ፣ ለመስጠት የአእምሮ ጥረት የሚጠይቅ ሲሆን ይህም ከቀን የሥራ ሰዓቱ 65% ይሆናል።

**3.7.2.** ስነልቦናዊ ጥረት

- **ሥራው የተለያዩ የጤና ችግር ያለባቸውንና ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ታካሚዎች በማገልገል ሂደትህይወትን ለማዳን በሚደረግ ጠረት የሚያጋጥመውን በጣም ከፍተኛ የመንፈስ መረበሽ እንዲሁም አስቸጋሪ ባህርይ ካለቸው ተጠቃሚዎች ጋር የሚፈጠረውን አለመግባባት በመታገስ፣ ለምሳሌ ለካንሰር፤ኤች አይቪ፤ለአእምሮ ህመም፣ የነርስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥራዎችን ለማሻሻል የሚደረግ ሂደት ያለውን ጫና በመቋቋም ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ የሥነ ልቦና ዝግጁነትን ይጠይቃል።**

**3.7.3** የዕይታ ጥረት፣

- ሥራው በየዕለቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ዕቅድ፣ የአፈጻጸም ሪፖርት መጻፍ እና መገምገም፣ የሥልጠና ማኑዋልና ለጥናትና ማሻሻያ

**የሚሆኑ ሃሳቦችን ለመጻፍ፣ መረጃ ለመተንተን፣ የመፍትሔ ሃሳቦችንና የታካሚውን አጠቃላይ መረጃ በጽሑፍ ለማዘጋጀት እንዲሁም የታማሚውን የጤና ችግር ለመለየት አተኩሮ ማየት፣ የተለያዩ ስራዎቸን እንደ መርፌ መዉጋት በተለያዩ ክፍሎች ቁስል መስፋት ክር ማዉጣት ለተለያዩ የሜዲካል ምርመራ የአይን ጥራት ላይ መሰረት ይጠየቃል የንድፈ ሃሳብ ትምህርትና የተግባር ልምምድ ለመስጠት የዕይታ ትኩረት የሚጠይቅ ሲሆን ከቀን የሥራ ሰዓቱ 30% ይሆናል።**

**3.7.4** የአካል ጥረት

- *ሥራው 25% በመቀመጥ፣ 20% በመቆም፣ 30% በእግር በመሄድ፣ 25% ጎንበስ ቀና በማለት ይከናወናል።*

**3.8.** የሥራ ሁኔታ

**3.8.1.** *ሥጋትና አደጋ*

- *ሥራው ሲከናወን በመርፌ መወጋት፣ በስለት መቆረጥ፣ በህመምተኛ ደምና ሌሎች የሰዉነት ፈሳሾች በመረጨት ህክምና ለሌላቸዉ በሽታዎች የመጋለጥና በተጨማሪም በትንፋሽ ለሚተላለፉ በሽታዎች የመዳረግ ስጋትና አደጋ የሚያጋጥምበት ነው።*

**3.8.2.** የሥራ አካባቢ ሁኔታ

- በደምና በሌሎች ከሰውነት በሚወጡ ፈሳሾች፣ እና በህመም ስቃይ ላይ ባሉበትና የተለያየ መጥፎ ሽታ ባለበት የሚከናወን ነው።

**3.9.** እውቀትና ክህሎት፣

**3.9.1.** ትምህርት

| የትምህርት ደረጃ | የትምህርት አይነት |
|---|---|
| የመጀመሪያ ድግሪ | በነርስንግ |

**3.9.2** *ሥራውን ለመጀመር የሚያስፈልግ የሥራ ልምድ*

| የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ | ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት |
|---|---|
| 3 ዓመት አገልግሎት | በነርሲንግ |

| የሥራ ትንተና ባለሙያ ሥም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| | | |

| የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |